# “ይህ ሁሉ ዛቻ ለኔ ብቻ አይመስለኝም፣ ለሁሉም ሰላማዊ ታጋዮችም እንጂ”

**- ወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ**



ታህሳስ 14 ቀን 2001 ዓ.ም ከሰዓት በኂላ በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነሩ ጽ/ቤት ተገኝቼ ማስጠንቀቂያ ከተነገረኝ እና ያው መልእክት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሲተላለፍ ስመለከት ያደረብኝ ስሜት ለመግለጽ ያዳግተኛል፡፡ ምንም እንኳን ይህን ሁኔታ ለመለወጥ ከማውቀው እና ከማምነው ነገር ውጭ የምናገረው ነገር ባይኖርም ጉዳዩ በሕዝብ መሃከል ጥያቄ–ች ማጫሩ አልቀረምና በጉዳዩ ላይ ግንዛቤን ለመፍጠር ይቺን ጽሑፍ ለመጻፍ ወስኛ ለሁ፡፡ምን አልባትም የመጨረሻ ቃሌ ይሆናል፡፡

በሽምግልናው ልጀምር፧ የሽምግልናው መሠረታዊ መንፈስ ሁለቱንም የሚያግባባ ስምምነት አምጥቶ እና የእርቅን መንፈስ ፈጥሮ የፖለቲካ ሂደቱን ማስቀጠል ነበር፡፡ ይህም በመሆኑ ነው ሂደቱ በርካታ ወራትን ሊወስድ የቻለው፡፡ በዚህም ውስጥ ምርጫ 1997 ዓ.ም ተከትሎ የተፈጠረውን ችግር በተመለከተ ያገር ሽማግሌ–ቹ አንዱን አጥፊ አንዱን ንጹህ በማድረግ መንገድ ሳይሆን እያንዳንዱ ወገን በወቅቱ ለተፈጠረው ችግር ሕዝቡን ይቅርታ ጠይቆ እና እርስ በርሱም ተጠያይቆ በመሰረታዊ ጉዳዮችም ያለውን የፖለቲካዊ አመለካከት ቁርጠኝነትን አረጋግጦ በእርቅ መንፈስ ወደፊት በጋራ ለመቀጠል በሚል አላማ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው ያሉዋቸውን ነጥቦች ለሁለቱም ወገኖች ሲያቀርቡ ሃሳቦችን ሲያለዋውጡና በተቻለም መጠን ለማለዘብም ሲሞክሩ ቆይተዋል፡፡

ከዚህም የተነሳ ይህ በመንግሥት ፈቃደኝነት ብቻ ሳይሆን ተሳትፎም ጭምር በሀገር ሽማግሌ–ቹ ሲደረግ የነበረው ሽምግልና ሁለቱም ወገኖች ሰጥተው እና ተቀብለው በሚያመጡት ማስማሚያ ሃሳብ /negotiated deal / በመድረስ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ በሂደቱ መንግሥትም ለሕገ መንግሥታዊ ሥርአቱ ያለውን ታማኝነት እንደገና እንደሚያረጋግጥ እና በ1997 ዓ.ም ምርጫ ጋር በተያያዘ በተፈጠረው ችግር ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎችን እና ቤተሰቦችን ለመካስ ተስማምቶ የነበረ ቢሆንም ውይይቱ እየቀጠለ ሲሄድና የፍርድ ቤቱ ክርክር ወደ ብይን በሚቃረብበት ወቅት በሽማግሌ–ቹ አስተባባሪ አማካይነት አንድ አሳዛኝ ሁኔታ ተነገረን፡፡ ይኸውም ሌላኛው ወገን እኛ ታሳሪ–ቹ ከሕዝብ እና ከመንግሥት ይቅርታ ከምንጠይቅበት ነጥብ ውጭ በተለይም መንግሥትን የሚመለከቱ የውይይት ነጥቦች ላይ መስማማት አይፈልጉም የሚል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በዚህም ደረጃ የውይይቱ አቅጣጫ የተመሰረተበት የእርቅ መንፈስ አልተቀየረም ነበር፡፡ ስለሆነም ሽማግሌ–ቹ ሌሎች የመግባቢያ ሃሳቦች ወደኂላ የተተዉ ቢሆንም በአገራችን ባህል ይቅር በመባባል መንፈስ የተቃኘውን ያንን ሰነድ ብንፈርም ጉዳዩ ባለበት ደረጃ እንደሚቆም ፋይሉም እንደሚዘጋ ገልጠው ሽምግልናውን ገፉበት ፡፡ ቃል በቃል በመግለጽም ጠቅላይ ሚኒስትሩ «ይህ ሰነድ ከተፈረመ የሥራ አስፈጻሚ ሥልጣኔን ተጠቅሜ ክሱ እንዲቋረጥ አደርጋለሁ» እንዳሉ አረጋገጡልን፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም «በአገሪቷ ውስጥ ከቅንጅት ጉዳይ ጋር በተያያዘ የታሰሩ እስረኞች በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደሚፈቱ፧በመንግሥት እና በቀድሞው ቅንጅት መሪ–ች መሃከልም የፖለቲካ ውይይት በቀጥታ እንደሚጀመር፧ የፓርቲው መሪ–ች ያለ ምንም ገደብ የፓርቲውን ሥራ እንደሚቀጥሉ» ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር፡፡ በተጨማሪም ይህ ሰነድ በማንኛውም መንገድ ለምንም አይነት ፕሮፓጋንዳ ጥቅም በሁለቱም ወገኖች እንደማይውል እና ሰነዱም የሚፈረመው ለሽማግሌ–ች እንደሆነ፧ ሽማግሌ–ችም በዚያ ላይ ተመስርተው የራሳቸውን ደብዳቤ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚፅፉ በሽማግሌ–ች፧ የተረጋገጠ መሆኑ ታሳቢ ሆኖ ሰነዱ ተፈርሟል፡፡ በርግጥም በዚህ ሰነድ ላይ እኔም እንደ አንድ ታሳሪ መፈረሜን ክጄ አላውቅም፡፡ በሽማግሌ–ቹም የእርቅ ማግባቢያ መንፈስ መሰረት በፖለቲካ የተቀሰቀሰውን ክስ ፖለቲካዊ እልባት ለመስጠት በማሰብ ለእርቅ ስል ከሌሎች የፓርቲው መሪ–ች ጋር ተስማምቼ ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በተጻፈው ሰነድ በሽማግሌ–ች አማካኝነት ይቅርታ ጠይቄአለሁ፡፡ይህ ብፈልግም ልለውጠው የማልችለው ሀቅ ነው፡፡

ከዚህ ስምምነት በኂላ ይጠበቅ የነበረው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሽማግሌ–ቹ አረጋግጠው በሰጡት ቃል መሰረት የክሱ መቋረጥ እና የፋይሉ መዘጋት ቢሆንም ሂደቱ ሌላ አዲስ መልክ ያዘ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመሩት አቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ክሱን ሳያቋርጥ ቀረ፡፡ ይልቁንም ተከሳሾቹ እድሜ ልክ ቅጣታችንን ተቀበልን፡፡ ከዚህ በኂላ እንግዲህ ታሪኩ በእኛ ስምምነት ሳይሆን በጠቅላይ ሚኒስትሩ ፈቃድ የተቃኘ

ነው፡፡ ጉዳዩም ብሎ ብሎ የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ለታሳሪ-ቹ በሰጡት ይቅርታ እኛ ከእስር በመፈታታችን ተገባደደ፡፡

እንግዲህ እንዲህ ያለ የተዥጎረጎረ መልክ ያለውን ውስብስብ ሂደት በመደበኛው የሕግ የይቅርታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት እንደቀረበ በዛውም አግባብ እንደተደመደመ ጉዳይ ብቻ ለማየት መሞከር አንድም እራስን ማሞኘት ነው ሌላም አለማወቅ፡፡

አንድ ተከሳሽ በሕጉ መሠረት የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ ያለበት ለጠቅላይ ሚነስትሩ ሳይሆን ለይቅርታ ቦርድ ነው፡፡ በእኛ ጉዳይ ለአገር ሽማግሌ-ች የፈረምነውን ሰነድ ለይቅርታ ቦርድ ያቀረቡት ጠቅላይ ሚነስትሩ ናቸው፡፡ ይቅርታውንም የጠየቁት እርሳቸው ናቸው ብሎ መከራከርም ይቻል ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን በሕጉ አግባብ የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ባለጉዳዩ፣ ጠበቃው ወይም ቤተዘመድ እንጂ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አይደለም፡፡ ጥያቄው መቅረብ የሚችለውም በጉዳዩ ፍርድ ቤት ፍርዱን እና ቅጣቱን አጠናቆ ከወሰነ በኋላ እንደሆነ በሕጉ ተመላክቷል፡፡ በእኛ ጉዳይ ከመነሻው ጉዳዩን በይቅርታ /pardon/ የመጨረስ ስምምነት ስላልነበረን ለሽማግሌ-ቹ የተፈረመው ሰነድ የተፈረመው ፍርድ ቤት በጉዳዩ የቅጣት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ እውነታ በመነሳት በዚህ በሕግ በተሰመረ አግባብ የይቅርታ ጥያቄ አላቀረብኩም፡፡ ሆኖም ግን በመጨረሻ በፕሬዝዳንቱ ለተሰጠው ይቅርታ መሠረት የሆነውን የአገር ሽማግሌ-ች ለእርቅ ሲሉ አግባብተው ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም ያስፈረሙንን ሰነድ ከነይዘቱ አልካድኩም ብሎ መናገሩ የቱ ላይ ነው ስህተቱ? የቱ ላይ ነው ወንጀሉ?

በውጭ አገር በጉዳዩ የተናገርኩትም ይህንኑ የሚገልጽ እና የሚያብራራ እንጂ ሌላ ምንም የተለየ ይዘት አልነበረውም፡፡ምን አልባት የተናገርኩት አላግባብ ተተርጉሞ ሊሆን እን ደሚችል እገምታለሁ፡፡

ይህ የእኔ አነጋገር የተዛባ ነው ቢባልስ ፖሊስ ጣቢያ በመጥሪያም ያለመጥሪያም ለመመላለስ ያበቃል?በፍጹም፡ ያስጠይቃል ቢባልስ በአገሪቱ ፕሬዝዳንት የተሰጠን ይቅርታ የሚያስነሳው እንዴት ይሆን? ይቅርታን የሚያስነሳስ ቢሆን ፌደራል ፖሊስ በየትኛው ህጋዊ ስልጣኑ ነው በጉዳዩ ምርመራ የሚያደርገው ማስጠንቀቂያስ የሚሰጠው?
ታህሳስ 1 ቀን 2001 ዓ.ም የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር የወረዳ 12 ፖሊስ አባላት የሆኑ ሁለት ፖሊሶች ቤቴ ድረስ በመላክ ቢሯቸው ድረስ እንድመጣ ሲጠሩኝ ስለ ፓርቲያችን ስለ አንድነት ለመወያየት ሊሆን ይችላል በሚል በጽ/ቤታቸው ተገኘቼ የተጠራሁት ከይቅርታው ጋር በተያያዘ መሆኑ ሲነገረኝ መጀመሪያ የጠየኩት ጥያቄ ፖሊስ በዚህ ጉዳይ ምን ስልጣን አለው የሚል ነበር፡፡ ምላሹ ግን በመደነቅ ፈገግታ የታጀበ ይሄ እኮ የአካዳሚ ውይይት አይደለም እንዲህ አይነት ጥያቄ ብትተይ ይሻልሻል የሚል ምላሽ ነበር፡፡ ለእነርሱ ያስፈገጋቸው፣ ያስገረማቸው ጉዳይ ግን እኔን ሁሌም የምኖርለት፣ የምቆምለት፣ አንዳንዴም የምታሠርለት እና የምፈታለት ታላቅ ቁምነገር ነው- የሕግ የበላይነት ወይም ሕገ መንግሥታዊነት፡፡

ሕገወጥነትን፣ ማንአለብኝነትን መቼም አልለምደውም፤ አልተባበረውም፡፡ ለዚህም ነው ታህሳስ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ፖሊ.ስ ኮሚሽነሩ በድጋሚ ያለ ሕጋዊ መጥሪያ በመልክተኛ ወደ ቢሯቸው ሲጠሩኝ በወቅቱ ሳልሄድ የቀረሁት፡፡ በእለቱ ከሰዓት በኋላ የሕግ መጥሪያ በደረሰኝ ጊዜ ግን ወደ ቢሯቸው ለመሄድ ደቂቃም አላጠፋሁ፤ በኮሚሽነሩ ቢሮ ስደርስ የጠበቀኝ እና መጥሪያው የሚገልጸው ለየቅል ቢሆንም፡፡ ኮሚሽነሩ በላኩልኝ መጥሪያ ላይ እንደተጠቀሰው ጥያቄ ሳይሆን ያቀረቡልኝ መመሪያ ነክ ማስፈራሪያ ነበር፤ ስዊድን የሰጠሽውን ቃል በሦስት ቀን ውስጥ ካላስተባበልሽ መንግሥት ይቅርታውን አንስቶ እሥር ቤት ይከትሻል የሚል፡፡

ይቅርታውን ማንሳት የሚችሉት እኮ የአገሪቱ ርእሰ ብሔር እንጂ እርስ- መንግሥት የሚሉት የሥራ አስፈጻሚ አካል አይደለም ለዛውም እርሱም ቢሆን ስርአት አለው ፡፡ የይቅርታ ይነሳ አቤቱታ ቀርቦ በ20 ቀናት ውስጥ ለባለጉዳዩ ደርሶ ቦርዱ ካመነበት ጥያቄው ለፕሬዝዳንቱ ቀርቦ ያኔ ይቅርታው ሊነሳ ይችላል እያልኩ ለኮሚሽነሩ ላስረዳቸው አስቤ ነበር፤አላደረኩትም፡፡ ንግግራቸውን መጨረሳቸውን አረጋግጬ ያለ ምንም ቃል ቢሯቸውን ጥዬ ወጣሁ፡፡

በእኔ እምነት ይሄ ሁሉ ከሕግ የወጣ ዛቻ እና ማስፈራሪያ እየደረሰብኝ ያለው ስለ ቃላት ጨዋታ ወይም ስለ ተዛባ እውነት ወይም ስለ ተጣሰ ሕግ አይመስለኝም፡፡ መልእክቱ ግልጽ ነው፤ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሰላማዊ ታጋዮች፡፡ በሰላማዊ እና ሕጋዊ ማእቀፍ ውስጥ የፖለቲካ ትግል ማድረግ የሚቻለው በሕገ መንግሥቱ በተሰመረው መሥመር ሳይሆን ገዢው አካል ወይም ግለሰቦች በፈቀዱት ብቻ የሚል፡፡ ለዚህ ደግሞ እሺ ወይም አ- ማለት ለእኔ እጅግ ከባድ ነው፡፡

-------

**ፎቶው የሚያሳየው በወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ የሚመራው ልዑክ በሰሜን አመሪካ በሲያትል ከተማ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ደማቅ አቀባበል ሲደረግለት ነው።**

**ኢትዮሚድያ**
December 27, 2008
Seattle, Washington
USA